# ሀሳብ የሚያጥረው ሰው የግለሰቦችን ስም በማጠልሸት ጊዜውን ይገፋል!!

**እውነቱ ዘለቀ** 01-24-17

የሰው ልጅ ከእንስሳት የሚለየው በቅጡ ማሰብ በመቻሉና የሚያስበውንና በውስጡ የሚያውጠነጥነውን ነገርም ወደ ተግባር ቀይሮ ለራሱ ሊስማማ በሚችል መልኩ ጥቅም ላይ ማዋሉ ጭምር ነው፣ ይህም ሆኖ ሁሉም የሰው ልጅ ተመሳሳይ የሆነ እሳቤና አተያይ ይኖረዋል ማለት አይደለም። አንዱ በተፈጥሮው ዴሞክራትና ቀና ሲሆን ሌላውኛው ደግሞ ፍጹም አምባገነንና ጠማማ ይሆናል፣ አንደኛው ሀቀኛ መሆኑን በተግባር ሲያረጋግጥ ሌላኛው የሀሰት ድር እያደራና የወሬ መአት ከዚህም ከዚያም እየለቃቀመ በማያገባው ጉዳይ ሳይቀር እየገባ የሰውን ማንነት ለማጠልሸት ሌት ተቀን ሲባዝን ይታያል።

ሰሞኑን የእኔን መጣጥፎች መነሻ በማድረግ ታጋይ ካህሳይ፣ ታዛቢ ይናገርና ቀለሙ በለጠ የተባሉ ጸሀፊዎች የአቶ ሲሳይን ስም በማንሳት ከእኔ ጋር ለማመሳሰል ከመሞከራቸውም በላይ ስማቸውን ለማጥፋት ምን ያህል እንደደከሙ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ታጋይ ካህሳይ በመግቢያቸው ላይ ጠቅለል ባለ መልኩ በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና በጸረ-ዴሞክራሲያዊ አመለካከት መካል በተለይም በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የትምክህትና የጠባብነት አሰተሳሰብ የበላይነት ካገኘ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ አሰመልክተው በሰጡት ማብራሪያ እኔም በአብዛኛው እስማመለሁ።

ብአዴን የጥልቅ ተሀድሶ መድረኩን ተጠቅሞ ሊፈታቸው ይገባል ባሏቸው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ችግሮችም እንዲሁ፣ የሀገራችንን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ስንመለከትም በተጨባጭ ችግር እየፈጠሩ ያሉት አስተሳሰቦች እነዚሁና የእነዚሁ አስተሳሰቦች ያልተገባ ጥምረት የፈጠረው መደናበር እንደሆነም አምናለሁ።

ከዚህ ውጭ በአጋጣሚ በተወሰኑ ሰዎች ላይ እየደረሰ ያለውን የስም ማጥፋት ሁኔታ በተለይም በአቶ ገዱ ላይ የተካሄደው የተቀናጀ ዘመቻን በምሳሌነት አንስቼ ሀሳቤን በግልጽ ለማራመድ ሞከርሁ እንጂ የማንም ተላላኪ ወይም ጠበቃ የመሆን ፍላጎት የለኝም። በታሪኬ እንዲህ አይነት ባህሪ እንደሌለኝም በቅርብ የሚያውቁኝ ሰዎች ምስክርነታቸውን ሊሰጡ ይችላሉ።

ሆኖም ይህን አጠቃላይ ገንዛቤ መሰረት በማድረግ የእኔን ጽሁፎች ይዘትና የአቶ ሲሳይን ስብዕና እና ፖለቲካዊ ግንዛቤ አስመልክተው የሰጡትን አስተያየት ስመለከት አሁንም በትክክል የተረዱን ወይም ሊረዱን የፈለጉ አልመሰለኝም። በእርግጥ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ የእርሰዎ አቀራረብ በተቻለ መጠን ጨዋነት የተንጸባረቀበት መሆኑንና የእኛ መነሻ ሀሳበብ ምን እንደሆነ ለማወቅ ካለዎት ፍላጎት የመነጨ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ፣ የሆነ ሆኖ እርሰዎ በሰጡት አስተያየትም ሆነ ባነሷቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ላይ ያለኝን ሀሳብ እንደሚከተለው ለማቅረብ እሞክራለሁ።

እኔ የትግራይ ተወላጅም ሆነ የህወሀት አባል ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ለሚሰራው መልካም ስራ ተገቢ ዋጋ ሊሰጠው ይገባል፣ በተቃራኒው ለራስ ሲቆርሱ … አይነት ነገር ተይዞ የሌላውን ህዝብ ድርሻ ማኮሰስ አሊያም ዋጋ ማሳጣት በምንም መልኩ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ባይ ነኝ። ይህንን መርህ ታሳቢ በማድረግም በአንዳንድ የትግራይ ተወላጆች የሚጻፉ ጽሁፎችን በድፍረት እተቻለሁ እንጂ መላው የትግራይ ህዝብን የምሰድብበትም ሆነ የምትችበት ሁኔታ የለም።

ችግሩ አሁንም ያለው የሚመስለኝ አንድ የትግራይ ተወላጅ ወይም ህወሀት እንደ ፖለቲካ ድርጅት በሚፈጥረው ስህተት ሲተች ሁሉም የትግራይ ህዝብ እንደተተቸ አድርጎ የመረዳት ጉዳይ ይመስለኛል። በሌላ በኩል እርስዎም ጥሩ አድርገው እንዳስቀመጡት "የዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ሃይሎች ቀዳሚ እምነታቸው ሁሉም ሰዎች በብሄር፤ በሃይማኖት፤ በፖለቲካ፤ በአኗኗር፤ በባህልና በሚከተሉት አስተሳሰብ እኩል ናቸው በአገራቸውም የየራሳቸው ልዩነት ቢኖራቸውም አብረው

ለመኖርና በጋራ ለማደግ የሚያስችሉ የጋራ እሴት አሉዋቸው ብለው ያምናሉ:: የህዝቦች በጋራ ተፋቅረውና ተማምነው መኖር የእደገት ዋስትና መሆኑ በፅናት አምነው ይሰራሉ::"

ሊረዱልኝ አልቻቻም ወይም አልፈቀዱም እንጂ እኔም እኮ እያልሁ ያለሁት ይኸንን ነው፣ እነዚህ የትግራይ ተወላጆች ነን እያሉ የሚጽፉትም ሆኑ ህወሀት እንደ ድርጅት የሌሎችን ህዝቦች አዎንታዊ ሚና በምንም መልኩ ወደ ጎን መተው ኢሊያም ማኮሰስ የለበትም ብቻ ሳይሆን ሁሉም ነገር በህወሀትና በትግራይ ህዝብ ጥረትና መስወአትነት ብቻ የተገኘ ነው የሚለውን አስተሳሰቡን ያስተካክሉ ነው።

ከዛ ባሻገር ቀደም ባለው ጽሁፌም ሆነ በአሁኑ ውሸት ያለበት አንድን ሀሳብ አራምጄም ሆነ አቅርቤ አላውቅም፣ ቀደም ሲል በኢህአዴግ ላይ የታዘብኳቸውን ድክመቶች ስጽፍም ሆነ በአሁኑ ወቅት የኢህአድግ አመራር ሆኜ አይደለም፣ እንደዛ ብየ ተናግሬም ሆነ ጽፌ አላውቅም።

በ1983 ዓ.ም ኢህአፓ ተጋብዞ ነበር ለሚሉት እርሰዎም አስተማማኝ የሆነ መረጃ ያለዎት አይመስለኝም፣ ቢኖረዎትማ ያንን ጠቅሰው ማቅረብ ይችሉ ነበር። ሆኖም እኔ ባለኝ መረጃ መሰረት አጠቃላይ ለተቃዋሚዎች የተሳተፉ ጥሪ ተላልፎ የነበረ መሆኑ ቢታወቅም ኢህአፓ እንደ ድርጅት እንዲሳተፍ ግን በኢህአዴግ አመራር ዘንድ ያን ያህል ፍላጎት አልነበረም።

ይህንን ሀቅ አስመልክተው የሽግግሩን ወቅት ፖለቲካዊ ሁኔታ በሚገባ መርምረው የጻፉት እነ ፕሮፌሰር አለም ሀብቱም ያረጋገጡት ጉዳይ ይኸን ነውና ለተጨማሪ ግንዛቤ የእሳቸውን ጽሁፎች ቢመለከቱ የእኔን ሀሳብ ውሸት ነው ለማለት አይደፍሩም ነበር። ከዛ ውጭ የትግራይ ህዝብና መሪ ድርጅቱ ላይ የተለየ ጥላቻም ሆነ አስተሳሰብ የለኝም ከላይ ለማለት እንደሞከርሁት በተወሰኑ ግለሰቦች አማካኝነት በትግራይ ህዝብ ስም የሚጻፈውን ነገር እርሰዎም እኮ ሲያስተባብሉ አልታዩም።

እንዳውም እርሰዎ ካሉት በተቃራኒው እኔ በጎንደርና አካባቢው ተከስቶ በነበረው ሁከትና ብጥብጥ አማካኝነት በደረሰው ጥፋት ሳቢያ ለተጎዱ ወገኖቻችን ተጠያቂው ገዥው ፓርቲ ብአዴን ኢህአዴግና የክልሉ መንግስት ነው በማለት በግልጽ ተችቻለሁ። ይህን ሁኔታ መቼም ከጽሁፌ ላያ ሳያገኙት ቀርተው አይመስለኝም፣ የትግራይ ሰዎች ብቻ ጥቃት ደረሰባቸው ብየ ግን አልጻፍሁም፣ ልጽፍም አልችልም።

ጥቃቱና ጉዳቱ በሁሉም ነዋሪዎች ላይ ነው የደረሰው የሚል እምነት ስላለኝ፣ እንዲሁም በትግራይ ተወላጆች ላይ በተለየ ሁኔታ እንደተቃጣ ጥቃት አድርጎ ከማራገብ ይልቅ በአካባቢው በሚኖሩ ቅማንቶችና አማሮች ላይ የደረሰ ጥቃት በመሆኑም ጭምር በአንድ ወገን ላይ የደረሰው ጉዳት ተደጋግሞ ኢሊያም ተጋኖ ሲነገርና የሌላው ተዳፍኖ ሲቀር የሚሰማው ሰው እንዳለም ልብ ሊባል ይገባል ነው እያልሁ ያለሁት።

በተረፈ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ብቻ ሳይሆን ከዛም በፊት የህወሀት የበላይነት በተግባር እየተስተዋለ ስለነበረ በጊዜ ሊታረም ይገባል የሚል እምነት ነበረኝ። ይህንን ሀቅ እናንተም በተሀድሶ ግምገማችሁ እንዳረጋገጣችሁት የህወሀት የበላይነት ቁልጭ ብሎ ይታይ እንደነበር ይህም ሁኔታ በእህት ድርጅቶች ሳይቀር ቅሬታ ፈጥሮ እንደነበር ግልጽ ነው። በምሳሌ እንዳስደግፈው ካስፈለገም  ታጋይ ካህሳይም ሆኑ ሌሎቹ ተቺዎች ዘንግተውት ወይም የተረሳ መስሏቸው ካልሆነ በስተቀር በጊዜው የህወሀት የበላይነት እንደነበረ የህወሀት ካድሬዎችና ከፍተኛ አመራሩ ጭምር በምሳሌ አስደግፈው ሲገመግሙ የኢህአዴግ ጽ/ቤት እኮ ኢህአዴግን ሳይሆን የህወሀት ጽ/ቤትን ነው የሚመስለው። ይኸ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች ደግሞ (በዋናነት የመከላከያ፣ የውጭ ጉዳይ፣ የደህንነት) መቀሌ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የትግራይ ክልል ቢሮዎች እስኪመስሉ ድረስ በህወሀት አባላትና በትግራይ ተወላጆች ተሞልተዋል በማለት ጭምር

አረጋግጦ ትንሽ ቆይተው የተወሰኑት ቀስ በቀስ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ቢደረግም የአሁኑን ሚኒስትር ደብረጽዮን ገ/ሚካኤልንና ዋና ዳይሬክተር ዘርአይ አስገዶምን ጨምሮ በርካታ የህወሀት ካድሬዎችና ከፍተኛ አመራሮች ወደ ትግራይ ብሔራዊ ክልል ሄደው በየደረጃው ተመድበው እንዲሰሩ መደረጉ ይታወቃል።

ከዚህ ውጭ እኔ የቱ ላይ ነው የዋሸሁትና የትግራይን ህዝብም ሆነ ህወሀትን በጅምላ ስማቸውን ለማጥፋት የሞከርሁት? የአቶ ታዛቢ ይናገር ድርቅና ግን በጣም የሚገርም ነው፣ ከአቶ ሲሳይ ጋር የግል ጠብ ወይም ጥላቻ ካለህ ሌላ ሰበብ ሳትፈልግ ከእሱ ጋር በቀጥታ ብትገጥም ሳይሻል አይቀርም፣ ይህም ቢሆን ሀሳብን በሀሳብ እንጂ የግለሰብ ተክለ ሰውነትን ያውም የሀሰት ውንጀላን መሰረት ባደረገ መልኩ እንደ ወረደ ማዥጎድጎድ ለራስህም የሚያሳፍር ይመስለኛል።

እርግጠኛ ነኝ ከስሜት ነጻ ሆኖ የሚያስብ ህሊና ካለህ አንድ ቀን በድርጊትህ ታፍርና ተጸጽተህ ጭምር አቶ ሲሳይንም ይቅርታ ትጠይቀው ይሆናል። የሰጠኸው መልስም ከአፈርሁ አይመልሰኝ አይነት እንጂ ሁሉም አባባሎችህ ከውሸት ፋብሪካ እየተቀዱ የወጡ ነገር ግን ስለ አቶ ሲሳይ የሰማኸቸውን ወይም ያገኘሀቸውን ምጥስጣሽ ማስረጃዎች ቆርጠህ በመቀጠል ለማቀራረብ የሞከርህባቸው እንደሆነ ይሰማኛል።

ለአንተ ከዚህ በላይ ቦታ መስጠትም ሆነ ዝረዝር መልስ ማቅረብ ተገቢ ነው ብየ ስለማላምን ከዚህ በላይ ማለት አልፈልግም፣ እውነተኛ ማንነትህ ሲታወቅ ግን የአንተም ጉድ አንድ ቀን ሊወጣ እንደሚችል መገመት አይከብደኝም። አቶ ቀለሙ በለጠ የተባለውማ ተራ አሉባልታ ይዞ ቀረበ እንጂ የረባ የሀሳብ ትግልም ሆነ ጨዋነት የተሞላበት ክርክር ስላላቀረበ ምናልባትም ቀጥታ አቶ ሲሳይ ላይ ስላተኮረ ስሜን ጠቀሰ ብየ እኔ እዚህ ላይ የምለው አይኖረኝም።

ቸር ይግጠመን!!